# ማጠቃለያ አጭር መግለጫ

## ዓለም አቀፍ ደረጃዎች (ስታንዳርዶች) በወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ጾታዊ ትንኮሳ ላይ

RESOURCE & SUPPORT HUB

UKaid from the British people

ይህ አጭር የማጠቃለያ መግለጫ የተዘጋጀው የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ጾታዊ ትንኮሳ ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን በተመለከተ አጠቃላይ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ታስቦ ነው። ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ጾታዊ ትንኮሳ የሚከሰተው ሰዎች ግለሰባዊ ስልጣናቸውን ያለአግባብ ሲጠቀሙ ነው። በተለያየ መንገድ በችግር ውስጥ ያሉ ቡድኖች አንዳንድ ጊዜ ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ጾታዊ ትንኮሳ ያጋጥማቸዋል። በወሲባዊ ብዝበዛ ጥቃት እና ጾታዊ ትንኮሳ በአብዛኛዉ ተጠቂ የሚሆኑት ሴቶችና ልጃገረዶች ናቸው። መድልዎ የሚደርስባቸውና የሚገለሉ ግለሰቦች ለምሳሌ በእድሜ፣ በዘር፣ በጾታ እና በአካል ጉዳት ምክንያት ለወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ጾታዊ ትንኮሳ ተጋላጭ ናቸው።

የተለያዩ ዐለም አቀፍ የልማት እና ሰብአዊ ዕርዳታ ድርጅቶች ስራቸዉን በሚሰሩበት ወቅት የማህበረሰብ አባላትን እና ሰራተኞችን ደህንነት ለመጠበቅ የሚያስችል በወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ጾታዊ ትንኮሳ ዙሪያ ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን (ስታንዳርዶችን) አዘጋጅተዋል። እነዚህን ደረጃዎች ተግባራዊ ማድረግ የልማት እና የሰብአዊ ድጋፍ ሥራዎችን ለሚያከናውኑ የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች አስፈላጊና ጠቃሚ ነው። ይህም ሰራተኞቻቸውን ለመጠበቅ እና ሰራተኞቻቸዉ ስራቸዉን በሚሰሩባቸው ማህበረሰቦች ውስጥ ምንም አይነት ጉዳት እንዳያደርሱ ለማረጋገጥ ይረዳቸዋል፡፡

### ዓለም አቀፍ ደረጃዎች (ስታንዳርዶች)

ወሲባዊ ብዝበዛ፥ ጥቃትና ጾታዊ ትንኮሳን በተመለከተ በአለም አቀፍ ደረጃ የወጡት ስታንዳርዶች 5 ሲሆኑ የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ሁሉም ድርጅቶች የልማትና የሰብኣዊ እርዳታ ሥራ በሚያከናውኑበት ጊዜ እንዲጠቀሙባቸው ያበረታታል፡፡

### ፩ የጥቃትና ጾታዊ ትንኮሳ ስምምነት/ቫዮለንስ ኤንድ ሀራስመንት ኮንቬንሽን 2019 (ቁጥር 190) እና ምክረ-ሀሳብ/ሪኮመንዴሽንስ ቁጥር 206[1]

**ይህ ደረጃ/ስታንዳርድ ለምን አስፈለገ?** መንግስታት፣ ግለሰቦች በስራ ላይ የሚያጋጥሟቸውን ጥቃቶች እና ትንኮሳዎች መፍታት የሚያስችል ዓለም አቀፍ መመሪያና ማዕቀፍ እንዲኖራቸዉ ለማድረግ ፡፡

**ይህ ስታንዳርድ ምንና ምንን ያካትታል?** ይህ ስታንዳርድ ግለሰቦችን በሥራ ላይ ጥቃት ወይም ትንኮሳ እንዳያጋጥማቸው ይጠብቃል፡፡ መንግስታት በማንኛውም የስራ ሁኔታ ጥቃትን እና ትንኮሳዎችን ለመከላከል እና ለማስወገድ ህጎችን እና ደንቦችን ማዘጋጀት አለባቸው፡፡ አሠሪዎች በሥራ ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን እና ትንኮሳዎችን በመለየት እና ምላሽ በመስጠት ላይ ያተኮረ ፖሊሲ ማውጣትና ስልጠና መስጠት አለባቸው፡፡ ሴቶች እና ሌሎች ለጥቃት እና ትንኮሳ ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ደህንነታቸውን ለማረጋገጥ ተጨማሪ ድጋፍ ይፈልጋሉ፡፡ ማንኛውም ሰው ጥቃት ወይም ትንኮሳ ካጋጠመው ሪፖርት እንዲያቀርብ እና ድጋፍ እንዲያገኝ አስተማማኝ እና ሚስጥራዊ የሆነ የግንኙነት ስርዓት መኖር አለበት ፡፡

1 https://www.ilo.org/global/publications/meeting-reports/WCMS_721160/lang--en/index.htm

*ስታንዳርዱ በማን ላይ ይተገበራል?* መንግሥትዎ ስምምነቱን ካፀደቀ የእርስዎ ድርጅት መስፈርቱን መከተልና መተግበር አለበት። ምንም እንኳን እርስዎ የሚኖሩበት አገረ-መንግስት ህጉን ባያፀድቀዉም ድርጅትዎ ሰራተኞቹን በስራ ላይ ጥቃት እና ትንኮሳ እንዳይደርስባቸው የመከላከል የሞራል ግዴታ አለበት ::

## ፪ የልማት ድጋፍ ሰጪ ኮሚቴ [2] በልማት ትብብር እና በሰብአዊ ድጋፍ ወሲባዊ ብዝበዛን፣ ጥቃትን እና ጾታዊ ትንኮሳን ለማስቆም የተሰጠ ምክረ-ሀሳብ[3]

*የስታንዳርዱ መኖር ለምን አስፈለገ?* ለልማት እና ለሰብአዊ ስራዎች ገንዘብ የሚሰጡ መንግስታት ወሲባዊ ብዝበዛን፣ ጥቃትን እና ጾታዊ ትንኮሳን ለመከላከል እና ምላሽ ለመስጠት እንዲችል ስራቸውን ደረጃውን የጠበቀ ለማድረግ ፍላጎት አድሮባቸዋል ::

*ስታንዳርዱ ምንና ምንን ያካትታል?* ይህ **ስታንዳርድ** በሕይወት የተረፉ እና በወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ጾታዊ ትንኮሳ ሰለባ የሆኑ ሰዎችን መብት፣ መሰረታዊ ፍላጎትና ዝንባሌ ቅድሚያ ይሰጣል። የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኙ ድርጅቶች ወሲባዊ ብዝበዛን፣ ጥቃትን እና ጾታዊ ትንኮሳን መፍታት/ማስቀረት የሚችል ፖሊሲ እና የስነምግባር ደንብ ሊኖራቸው ይገባል። ሪፖርት ማድረግ ለሚፈልግ ሁሉ ምስጢራዊ እና ስም-አልባ የሪፖርት ስርዓቶች መኖር አለባቸው:: ይህ የአንድ መስሪያ ቤት ሰራተኞችን እና የማህበረሰብ አባላትን ያካትታል:: ድርጅቶች የሚያደርጉትን የጥንቃቄና የከለላ ስራ መዝግበዉ ማስቀመጥ አለባቸዉ። ይህም ስኬቶቻቸውን ለመከታተል እና ምን ማሻሻል እንዳለባቸዉ ለማሰብ ያስችላቸዋል።

*ስታንዳርዱ በማን ላይ ይተገበራል?* የልማት ድጋፍ ኮሚቴ አባል የሆኑ መንግስታት እና ከእነርሱ ጋር የሚሰራ ማንኛውም ድርጅት ይህንን *ስታንዳርድ* መከተል አለበት:: የልማት ድጋፍ ኮሚቴ አባል ያልሆኑ መንግስታትም *ስታንዳርዱን* እንዲከተሉ ይበረታታሉ::

## ፫ የኢንተር ኤጀንሲ ቋሚ ኮሚቴ ዝቅተኛ የአሠራር **ስታንዳርዶች**፡-ከወሲባዊ ብዝበዛ እና በገዛ ሠራተኛ ከሚፈፀም ጥቃት መከላከል።[4]

*ይህ ስታንዳርድ ለምን አስፈለገ?* **ስታንዳርዱ ያስፈለገው** የተባበሩት መንግስታት እና አጋሮቻቸው የራሳቸውን ሰራተኞች እና የማህበረሰብ አባላትን በሚሰሩበት ቦታ ወሲባዊ ብዝበዛ እና ጥቃት እንዳይደርስባቸው የሚጠብቁበትን መንገድ ደረጃውን የጠበቀ ለማድረግ ሲባል ነዉ:: ይህ **ስታንዳርድ** ጾታዊ ትንኮሳን አያካትትም።

*መስፈርቱ ምንና ምንን ያካትታል?* ይህ **ስታንዳርድ** የተባበሩት መንግስታት እና አጋሮቻቸው ወሲባዊ ብዝበዛን እና ጥቃትን ለመከላከል ፖሊሲ እንዲኖራቸው ያስገድዳል:: ተመድና አጋሮቹ በየአካባቢዉ የሚሰሩ የተባበሩት መንግስታት ጽ/ቤቶች እና አጋሮቻቸው ወሲባዊ ብዝበዛን እና ጥቃትን ለመከላከል ስለሚወስዷቸው እርምጃዎች ለአካባቢው ማህበረሰብ ማሳወቅ አለባቸው:: እነዚህ እርምጃዎች የማህበረሰብ አባላትን እና ሰራተኞችን ጨምሮ ማንኛውም ሰው ባህሉን በጠበቀ መልኩ ያለውን አሳሳቢ ጉዳይ ሪፖርት እንዲያደርግ እና ድጋፍ እንዲያገኝ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋትን፣ የሥራ ቅጥር ሂደቶች ትክክለኛ ሰዎችን እንዲለዩ ማረጋገጥን እና ደረጃውን እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንደሚቻል የሰራተኞች ስልጠና መስጠትን የሚያካትቱ ናቸው ::

2 የኢኮኖሚ ትብብር እና ልማት ድርጅት (ኦ.ሲ.ዲ.) ከመንግስት ፣ ፖሊሲ አውጪዎችና ዜጎች ጋር እኩልነትን እና ዕድሎችን ሁሉ የሚያጎለብቱ ፖሊሲዎችን እና ዓለም አቀፋዊ ደረጃዎችን ለማዳበር የሚሰራ አለም አቀፍ ድርጅት ነው :: OECD በዓለም ላይ ካሉ ታላላቅ የልማት ዕርዳታ አቅራቢዎች ጋር አንድ የሚያደርግ የልማት ድጋፍ ኮሚቴ (DAC) አለው። ይህም ገንዘብ እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል ለመከታተል ፣ ደረጃዎችን ማዘጋጀት እና በልማት ዕርዳታ ላይ የአባላትን ሥራ መከታተል :: DAC በአሁኑ ጊዜ 30 DAC አባላት አሉት:: https://www.oecd.org/dac/development-assistance-committee/

3 http://www.oecd.org/officialdocuments/publicdisplaydocumentpdf/?cote=DCD/DAC(2019)31/FINAL&docLanguage=En

4 https://interagencystandingcommittee.org/system/files/3_minimum_operating_standards_mos-psea.pdf

**ስታንዳርዱ በማን ላይ ይተገበራል?** ሁሉም የተባበሩት መንግስታት ሰራተኞች እና ከእነሱ ጋር በአጋርነት የሚሰራ ማንኛውም ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል ፡፡ ከተባበሩት መንግስታት ጋር አጋር ከሆኑ፤ ወሲባዊ ብዝበዛን እና ጥቃትን ለመከላከል እነዚህን የአሰራር ደረጃዎች ለመከተል መስማማት አለብዎት ፡፡

## ፬ ቁልፍ የሰብዊነት ስታንዳርዶች በጥራትና ተጠያቂነት ላይ (ኮር ሁማኒቴሪያን ስታንዳርድስ)[5]

**ይህ ስታንዳርድ ለምን አስፈለገ?** ይህ ስታንዳርድ በችግር ለተጎዱ ማህበረሰቦች ሰብዓዊ ዕርዳታን ለማድረስ የጋራ አካሄድን/ዘዴን ያቀርባል፡፡ በተጨማሪም ወሲባዊ ብዝበዛን፣ ጥቃትን እና ጾታዊ ትንኮሳን እንዴት መከላከል እና ምላሽ መስጠት እንደሚቻል ያጠቃልላል።

**ስታንዳርዱ ምንና ምንን ያካትታል?** ይህ መመዘኛ ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ጾታዊ ትንኮሳ አደጋዎች በድርጅቶች እና በፕሮግራሞቻቸው እንቅስቃሴ ውስጥ ተለይተው መፍትሄ እንዲያገኙ ይጠይቃል፡፡ ድርጅቶች ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃትን እና ጾታዊ ትንኮሳን ለመከላከል እና ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉ ፖሊሲዎች ሊኖሯቸው ይገባል። ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ጾታዊ ትንኮሳን ለመከላከል ለማህበረሰቡ የድርጅቱን አሰራር ማሳወቅ ተገቢ ነዉ። ማህበረሰቡ ሪፖርት ማድረግ እንዲችል የሪፖርት ማድረጊያ ስርዓቶች መኖር አለባቸው። የሪፖርት እና የምርመራ ሂደቶች ለተጎጂዎች እና ከጥቃት ለተረፉ ሰዎች ደህንነት፣ መሰረታዊ ፍላጎቶች ቅድሚያ መስጠት አለባቸዉ፡፡

**ስታንዳርዱ በማን ላይ ይተገበራል?** በችግር የተጎዱ ማህበረሰቦችን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚደግፉ ድርጅቶችን ይመለከታል፡፡ የጥራት እና የተጠያቂነት ዋና ሰብዓዊ ደረጃ ለሰብዓዊ ሥራ የተጻፈ/የተዘጋጀ ቢሆንም የልማት ሥራውን የሚያከናውን ማንኛውም አካል ሊጠቀምበት ይችላል፡፡

## ፭ ሕፃናትን ከአደጋ ለመጠበቅ የሚያስችሉ ዓለም አቀፍ የሕፃናት ደህንነት ጥበቃ ደረጃዎች[6]

**ይህ ስታንዳርድ ለምን አስፈለገ?** ወሲባዊ ብዝበዛ እና ጥቃትን ጨምሮ ሕፃናትን ከተለያዩ በሰብአዊነት ወይም ከልማት ዕርዳታ ጋር በተያያዘ ከሚያጋጥማቸዉ በደሎች ሁሉ ለመጠበቅ፡፡

**ስታንዳርዱ ምንና ምንን ያካትታል?** ይህ ስታንዳርድ ከሕፃናት ጋር በሥራ የሚገናኙ ድርጅቶች ሁሉ የሕፃናት ደህንነት ጥበቃ ፖሊሲ እንዲዘጋጅላቸው ይጠይቃል፡፡ ይህ ደረጃ ማንኛውም ከህጻናት ጋር የሚሰራ አካል በሕፃናት ጥበቃና ከለላ ላይ የሰለጠነ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ድርጅቶች በሁሉም የድርጅታዊ እንቅስቃሴዎች እና ሂደቶች ውስጥ የሕፃናት ደህንነት ጥበቃ እርምጃዎችን ማካተት አለባቸው። የሪፖርት ማድረጊያ ሥርዓቶች አንድን አሳሳቢ ነገር/ጉዳይ ሪፖርት ማድረግ ለሚፈልግ ማንኛውም ሰው በተለይም ለሕፃናት በቀላሉ የሚገኙና ምቹ መሆን አለባቸው ፡፡

**ስታንዳርዱ በማን ላይ ይተገበራል?** እነዚህ መመዘኛዎች ለማንኛውም ድርጅት በፈቃደኝነት የሚሰሩ ናቸው፡፡ ነገር ግን በተለየ ሁኔታ ሥራዎቻቸው ሕፃናትን የሚያሳትፉ ወይም በሕፃናት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ድርጅቶችን ይመለከታል ፡፡

5 https://corehumanitarianstandard.org/the-standard
6 https://www.keepingchildrensafe.global/wp-content/uploads/2020/02/KCS-CS-Standards-ENG-200218.pdf

## ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን ከራስ አውድ ጋር ማጣጣም፡- የእኔ ድርጅት እነዚህን ደረጃዎች እንዴት ተግባራዊ ማድረግ አለበት?

1. **በድርጅቴ ውስጥ ስለ ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ጾታዊ ትንኮሳ የተለየ ዕውቀት ከሌለኝ ምን ማድረግ እችላለሁ?**
   - ከሚያውቁት ኔትዎርክ ይማሩ። ስለ ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ጾታዊ ትንኮሳ ጉዳዮች የሚያውቅ ሌላ በቅርብ ያለ ድርጅት ይፈልጉ እና ከእነሱ ትኩረቶትን በሚስቡ ጉዳዮች ለመማር ጉብኝት ያዘጋጁ ፡፡
   - አስፈላጊ ከሆነ ከእርዳታ ሰጭዎች (ለጋሽ ድርጅቶች) ድጋፍ ይጠይቁ፡፡ በወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ጾታዊ ትንኮሳ ፖሊሲዎችና ሥርዓቶች መኖራቸው የገንዘብ ድጋፍ ለመቀበል የተለመደ መስፈርት እየሆነ መጥቷል፡፡ ለጋሾች በወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ጾታዊ ትንኮሳ ላይ እርስዎን ለመደገፍ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን መሥራትና የስልጠና እድሎችን መስጠት ይችሉ ይሆናል፡፡

2. **አንዳንድ የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ጾታዊ ትንኮሳ ዓይነቶች በአገሬ ውስጥ ህጋዊ ከሆኑ ምን ማድረግ አለብኝ?**
   - በብዙ አገሮች ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ጾታዊ ትንኮሳ በሕጉ መሠረት ሙሉ በሙሉ አልተሸፈነም፡፡ የእርስዎ ድርጅት አሁንም ቢሆን ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ጾታዊ ትንኮሳን በተሟላ መልኩ መፍታት ይችላል፡፡ ለምሳሌ፣ የስራ ላይ ጾታዊ ትንኮሳ ህጋዊ ከሆነ የድርጅትዎ የስነምግባር ደንብ አሁንም ወሲባዊ ትንኮሳዎችን ሊሸፍን ይችላል፡፡

3. **ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ጾታዊ ትንኮሳን ከሥራዬ ጋር ለማዋሃድ እንዴት መጀመር እችላለሁ?**
   - የሰዎች ደህንነት እንዲጠበቅ ለማድረግ አስቀድመው ስለሚሠሩት ሥራ ያስቡ፡፡ የሰዎችን ደህንነት እንዴት መጠበቅ እንደሚችሉ በተመለከተ ቀደም ሲል በድርጅትዎ እሴቶች ውስጥ የተካተተ ሊኖርዎት ይችላል። ድርጅትዎ ሰራተኞችን ለማበረታታት ወይም ለመቅጣት የሚፈልገውን ባህሪ ወደሚያካትት ቀላል የስነምግባር ደንብ ውስጥ ያስፋፉ፡፡
   - የሌሎች ድርጅቶችን ፖሊሲ ይመልከቱ። በድርጅትዎ በቀላሉ ሊያዋህዱ የሚችሏቸውን አንዳንድ ሂደቶች ይለዩ። ከጊዜ በኋላ ለማሳካት የሚሰሩዋቸውን ሌሎች ሂደቶችና ተግባሮች ይለዩ፡፡
   - በራስዎ ድርጅት ውስጥ ሊኖሩ የሚችሉትን አደጋዎች መገምገም ይጀምሩ፤ እናም እነሱን ለመቅረፍ መንገዶችን ይፈልጉ፡፡ የራስዎ ሰራተኞች ሊገጥሟቸው ስለሚችሏቸው አደጋዎች፣ ሰራተኞችን እንዴት እንደሚመለምሉ፣ በሚሰሩባቸው ማህበረሰቦች ላይ የሚደርሱ አደጋዎችን እና መርሃግብሮችን በሚነድፉበት ጊዜ ሊታሰብባቸው ስለሚገቡ ስጋቶች ያስቡ፡፡

4. **በራሴ ሥራ ውስጥ ስለ ኃይል/ሥልጣን እና ልዩ መብት እንዴት አስባለሁ?**
   - የአንድ ሰው ፆታ፣ ዕድሜ፣ ዘር፣ የአካል ጉዳት ወይም ጾታዊ ባህርይ በሰዉዬው ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራሉ። የሚከተሉት ጥያቄዎች በስራዎ ውስጥ ስላለው ኃይል እና ልዩ መብት ለማሰብ ጠቃሚ መነሻ ነጥብ ናቸው:-
     - በእድሜ ፣ በዘር ወይም በፆታ (ወይም በእነዚህ ጥምረቶች) ከሌሎች ይልቅ ልጠቀም የምችልበት ሁኔታ የሚፈጠረው መቼ ነው?
     - አካላዊ ቁመናዬ ሌሎች እኔን እንዴት እንደሚቀበሉኝ ተጽዕኖ ሊያሳድርብኝ ይችላል?
     - ግለሰቦች በምንም ምክንያት እንዳይገለሉ እና እኩል ዕድሎች እንዲሰጣቸው እንዴት ማረጋገጥ እችላለሁ?
   - ኃይል እና ልዩ መብት በግንኙነቶችዎ እና ከማህበረሰቦች እና ከራስዎ ሰራተኞች ጋር በሚሰሩት ስራዎችዎ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራሉ፡፡ በኃይል እና በልዩ መብት ላይ ሲታሰብ ሁለቱንም ከግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው ፡፡

**5. በአከባቢዬ ውስጥ ምን ዓይነት የድጋፍ አገልግሎቶች እንዳሉ ካላወቅኩ ምን ማድረግ እችላለሁ?**

- በሴቶች ፣ በቤተሰብ እና በልጆች ወይም በወጣቶች ጉዳይ የሚሠራውን በአካባቢዎ የሚገኘውን ቢሮ ያነጋግሩ ። በአካባቢያዊ ድጋፍ አገልግሎቶች ላይ መረጃ ሊሰጡዎት ይችላሉ፡፡ እንዲሁም አገልግሎቶችን ለይቶ ለማወቅ ሊረዳዎ የሚችል የአካባቢ መንግሥት ተወካይን ዝርዝር የአድረሻ መረጃ ሊሰጡዎት ይችላሉ፡፡
- በአከባቢዎ ውስጥ መደበኛ እና መደበኛ ያልሆኑ አገልግሎቶችን ይለዩ፡፡ አካባቢያዊ ድርጅቶችን እና የሴቶች ቡድኖች በመጠየቅ እንደዚሁም ተጠቃሚዎቻቸውን ወዴት እንደሚለኩ (ሪፈር እንደሚሉ) በማወቅ ይህንን ሊያደርጉ ይችላሉ። እንዲሁም ማህበረሰቡን ለእርዳታ ወደ ማን እንደሚሄዱ መጠየቅ ይችላሉ፡፡ የትኞቹ እምነት የሚጣልባቸው እንደሆኑ ለማወቅ በአገልግሎቱ ላይ አስተያየታቸውን ይጠይቁ፡፡

**6. አንዳንድ ዓለም አቀፍ ደረጃዎች ከማህበረሰብ እሴቶች እና እምነቶች ጋር የሚጋጩ ቢሆንስ?**

- በማህበረሰቡ ውስጥ ወሲባዊ ብዝበዛ ጥቃት እና ጾታዊ ትንኮሳ ምን ማለት እንደሆነ ግንዛቤን ያሳድጉ፡፡ ለዚህ ችግር የተጋለጡትን እንዴት እንደጎዳቸው ያስረዱ፡፡ ለወሲባዊ ብዝበዛ ጥቃት እና ጾታዊ ትንኮሳ ማን በጣም ተጋላጭ እንደሆነ ማህበረሰቦች እንዲለዩ ያድርጉ ።
- የማህበረሰብ አባላት ህዝብን ለመጠበቅ አስፈላጊ እንደሆኑ የሚያምኑባቸውን ነባር ማህበራዊ ህጎች እና ልምዶች እንዲለዩ ይርዷቸው፡፡ ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ቡድኖችን መጠበቅ እና መደገፍ አስፈላጊ የሚሆንበትን ምክንያቶች ለመለየት ከማህበረሰቡ ጋር ይስሩ፡፡ እነዚህ ውይይቶች በሂደት የሰዎችን አመለካከት ለመለወጥ አስፈላጊ ናቸው፡፡ የሰዎች አመለካከቶች እና ባህሪዎች ወዲያውኑ ሲለወጡ ካላዩ ተስፋ አይቁረጡ፡፡ ይህ የማህበረሰብ ማህበራዊ ደንቦችን እና ልማዶችን ስለመቀየር አይደለም፡፡ ድርጅትዎ በሰዎች ላይ ጉዳት የማያደርስ መሆኑን ማረጋገጥ ነው። ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ጾታዊ ትንኮሳ ምን ማለት እንደሆነ እና በማን ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ግንዛቤ በማስጨበጥ የእርስዎ ድርጅት ማህበረሰቦች ጉዳዩን ለይተው እንዲያውቁት እና ሪፖርት እንዲያደርጉ ይደግፋል፡፡